# ኢትዮጵያና ጎንደር፤

እንደሚታወቀው ሀገራችን የረጅም ጊዜ የታሪክ ገጽታ እንዳላት በእኛ በሃገሬው ሰዎች ብቻ ሳይሆን በዓለም ደረጃ በቀዳሚነት የታወቀ ነው። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በጎንደር ክፍለ ሀገር ውስጥ የተፈጠረውን ሕዝባዊ የማንነትና የሕግ የበላይነት ጥያቄ አስመልክቶ ከሚደረገው ወቅታዊ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ

- **ኢትዮጵያና ጎንደር፤**
- **ወልቃይትና ጎንደር፤**
- **ትግራይና ጎንደር፤** በሚሉ ርዕሶች ለአንባብያን በአጭር በአጭሩ የቀረበ ነው።

ጎንደር ከላስታው ሥረዎ መንግሥት በኋላ የሀገራችን ማዕከላዊ መንግሥት መናገሻ ከተማ ሁና ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ ያገለገለች ብዙ መጽሐፍተ ሕግጋት የተደነገገባት፣ ፍትሕህ ርዕትህ የታወጀባት፣ ሥርዓተ መንግሥት የቀናባት፣ መጽሐፈ ሃይማኖት የተተረጎመባት፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተመሠረተባት፣ ስነ ጽሑፍ፣ ዕደ ጥበብና ኪነ ጥበባት የተራቀቀባት፣ ሁሉም የሀገራችን ዜጎችን እንደ ጊዜ ግብሩ ሁኔታ የተስተናገዱባት፣ የኢትዮጵያ የግዛት አንድነት አካላዊ ገጽታ መልክና ቅርጽ እንዲይዝ የተደረገባት፣ መልካ ምድራዊ አቀማመጧ በሰው እጅ የታነጹ በሚመስሉ የተፈጥሮ ተራሮች የተከበበች፣ ብርቅየ የዱር አራዊት የለመዱባት፣ ተከዜ፣ በሸሎ፣ አንገረብና አባይ ወንዞች እንዲሁም ጣና ሀይቅ በራቱም አቅጣጫ በቅርብ እርቀት የሚገኙባትና የሚያዋስኗት፤ ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ የአየር ንብረት በተመጣጣኝ ሁኔታ የሚፈራረቅባት፣ ቀንድ ከብት የሚረባባት፣ የቅባት እህል፣ የጥጥ ምርት በገፍ የሚታፈስባት፣ በሃይማኖት የተሰበከ በምግባር የቀና፣ በባህሉ የኮራ፣ በእንግዳ ተቀባይነትን የእምነቱ ክፍል አድርጎ የሚኖር፣ በሀገር ወዳድነቱ ሞቱን የሚመርጥ አርበኛ፣ገራ ሸንተረሩን ፈቅፍቆ የሚያርስ አምራች ገበሬ፣ ማኀበራዊ ኑሮን ደስታና ሐዘን በባህላዊ ሥራዓት በኀብረት ማሳለፍ የሚወድ ፈጣሪውን ፈሪ ሰውን አክባሪ ቅን ሕዝብ የሚኖርባት ታሪካዊ የሀገራችን ኢትዮጵያ ክፍል ናት።

የሀገራችን የሺዎች ዘመን ታሪክን እዚህ ላይ ለመተንተን ጊዜው አይደለምና ወቅታዊ የሕዝብ የማንነት ጥያቄን አስከትሎ የሚደርገውን እንቅስቃሴ ከታሪክ ጋር አያይዞ ከማቅረብ አንጻር ከዘመነ መሣፍንት የታሪክ ገጽታ ጀምሮ ያለውን በጣም በአጭሩ በአስረጀነት እደሚከተለው ቀርቧል።

በአትዮጵያ የጎንደር ማዕከላዊ ንጉሠ ነገሥታዊ መነግሥት እየተዳከመ ከመጣ በኋላ በየክፍለ ሀገር የነበሩት መሣፍንት በራሳቸው ክልልላዊ ግዛት ብቻ በመወሰን የራሳቸውን ጦር በማጠናከር እራሳቸውን በሥልጣን ኮርቻ ላይ ጭነው ለሰባ ስምንት ዓመታት ሀገራችን ከማንኛውም የልማት፣ የእድገት እና የአንድነት ማዕከላዊ አስተዳደር አመራር ተለይታ ማንነቷ ተረስቶ የመሣፍንት የርስበርስ ጦርነት ኀልብቶ ሀገሪቱ በከፍተኛ የጥፋት አዙሪት ውስጥ ገብታ ብዙ መዋለ ንዋይና የሰው ሕይዎት በከንቱ የጠፋበት ዘመን ነው።

ሀገራችን በዚህ በዋዥቀ መስመር ላይ ሆና ሕልውናዋ በመጥፋትና በመደብዘዝ ላይ በነበረበት በዚያ ክፉ ዘመን ወቅት፤ ከማኀበረ ሥላሴ ገዳም መንፈስዊ ትምህርታቸውን አቋርጠው ድንገት ሳይታሰብ ቋረኛው ካሣ በሽፍትነት ተነሱ። ደጃዝማች ካሳ ኃይሉ/አባ ታጠቅ/ እራሳቸውን በሽፍትነት እያጠናከሩ፣ ከሚያርሰው ገበሬ ጋር እየቆፈሩ፣ ከሚዘምተው ጋር በግንባር እየመሩ፣ ያለው ለሌለው እንዲያካፍል መመሪያ እየሰጡ፤ ማዕረግ ዝና እና ክብር ሳያኀብጣቸው እራሳቸውን የተግባራት ሁሉ ምሣሌ በማድረግ ያለ እረፍት ስልሳና ሰባ ሺህ ጦር በባዶ እግራቸው እየመሩ ድፍን የኢትዮጵያን ጋራውን እና ሸንተረሩን ወጥተው ወርደው የመከራ ጽዋንና እልክ አስጨረሽ የሆነውን ድካም ሁሉ ተቋቁመው፣ በየጎጡ እራሱን አንግሦ እየተጨፋጨፈ ለሀገሩ የጥፋት መቃብር ሲቆፍር እና የነበረችውን ኢትዮጵያን

እንዳልነበረች ያደረገውን የመሣፈንታትና የሽፍታ ዘመን ሁሉ በአስደናቂ የጦር ሜዳ ጀብዱ ድል አድርገው፣ ኢትዮጵያን ለሰባ ሰባት ዓመት ከተቀበረችበት አዘቅት ውስጥ አውጥተው እንደገና አንድነቷን አስከብረው ዳር ደንበሯን አረጋግጠው አቆሟት። ቀጥሎም አፄ ቴዎድሮስ ንጉሰ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ።

ጥንት የነበረችው የሺዎች ባለታሪክ ኢትዮጵያ በዘመነ መሣፍንት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ለአንድ ምዕት ዓመት ስትዛቅጥና እየደበዘዘች ለመጥፋት በተቃረበችበት ወቅት፤ ዛሬ ላይ ቆም ብለን የምንኮራባትን የምንመካባትን፣ በብሔር ብሔረሰቦች የተጌጠች፣ ስሟን ጠርተን የማንጠግበውን የዓለም ታሪክ ማስታዎሻ የሆነችውን ሀገራችን ኢትዮጵያን ማን እና እነማን ያለ እረፍትና ያለመሰልቸት በመጨረሻም እራሱን አሳልፎ እስከመስጠት በደረሰ መስዋትነት መልሶ እንዳቆማት በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ዳግማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ቴዎድሮስ መሪ ዓላማ እና እቅድ፤ ኢትዮጵያ በሥልጣኔ የቀናች፣ ዳር ደንበርዋ በሰለጠኑ ወታደሮችና የጦር መሣሪያ የታጠረች አንድነቷ የተጠበቀ ገናና ሀገር እንድትሆን ከማቀድ በተጨማሪ፤ የበለጠ የግዛት ተስፋፊነት ስሜት ነበራቸው። በየመናዊ አረቦች ላይ የነበራቸው አመጽ፤ በሌላ አቅጣጫ ለኢየሩሳሌም  የነበራቸው ናፍቆት፤ በጊዜው ከነበረው ከገናናው የንግሥት ቪክቶሪያ የንግሊዝ መንግሥት፤ እንዲሁም ከናፓልዮ 4ኛው የፈረንሳይ ንጉሥ ጋር ያደርጉት የነበረው የወዳጅነት ፍለጋ መጻጻፍ ሁሉ አፄ ቴዎድሮስ ዛሬ በእኛ ዘመን በየምክንያቱ እንደ ቂጣ እየተኮረመች ያነሰችውን ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ከዚህ የሰፋች ገናና ኢትዮጵያን የመገንባት ሰፊ ርዐይ ርሁቅ ምኞት እንደነበራቸው እንገነዘባለን። የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም እጮኛ እየተባለ የሚቀኘላቸው በዚህ ምክንያት ነው።

የዛሬን አያድርገውና ሀገራችን ኢትዮጵያ መካከለኛውን ምሥራቅ ለመቆጣጠር ምቹ ማማ የሆነ ስሜናዊ መልክአ ምድርና የባህር በር የነበራት ሀገር እንደመሆንዋ መጠን በተለይም እንግሊዝ ሀገር በምጵዋ በኩል ቆንስላዎችን እየላከች በሰላይነት ታስቀምጥ ነበር። በአፄ ቴዎደሮስ ዘመን ከተላኩት መካከል ቀዳሚዎቹ ጆን ቤልና ፕላውዴን የሚባሉት ሲሆኑ፤ የንጉሡ ድል አድራጊነትና ገናናነት እየተስፋፉ በመጣበት ወቅት፤ ጆን ቤል የመጀመሪያው የንጉሡ ቀራቢ ሆነ።

ጆን ቤልና ፕላውዴን አፄ ቴዎድሮስ ለሀገር አንድነት ማዕከላዊ  አስተዳደር ለሥልጣኔና እደገት ታላቅ ጉጉት ያላቸው፤ ይህንን ለማደናቀፍ በሚነሳ ላይ ጨካኝ የሆኑ፤ ድሃ የተጎሳቀለ ያጣ የነጣ ሰው ሲያዩ ርህሩህነታቸው ወደር የሌለው፤ ዳኝነትና ፍርድ የማያጓድሉ፣ ከልክ ያለፈ ከመጠን የዘለለ ዝናን እና ክብርን የማይፈልጉ፣ ሥርቆ የማሥራት ባህልን ያዳበሩ ሃይማኖተኛ መሆናቸውን በቀላሉ ለመረዳት ጊዜ አልወሰደባቸውም። ሁለቱም የንግሊዝ ቆንስላዎች አፄ ቴዎድሮስን እጅግ በጣም ቀራቢና አማካሪ ሆኑ። አፄ ቴውድሮስም ስለ ገናናው ስለ እንግሊዝ መንግሥታዊ መዋቅር፣ ፍርድ አሰጣጥና ሥልጣኔ አዘውትሮ በመጠየቅ ባገኙት መረዳት፤ በእንግሊዙ የቪክቶሪያው መንግሥት ሥልጣኔ ቀልባቸው ፍጹም ተሳበ። ከሕዝባቸው ንቃተ ኅሊና ጋር ባለተመጣጠነ መልኩ ሰፊ ርዐይ ሰንቀው ሀገራቸው ኢትዮጵያ፣ እንግሊዝ ሀገር ባለችበት መንገድ እንድትራመድ እጅግ በጣም እሩቅ አሳቢ ሆኑ።

በሁለቱ እንግሊዞች አማካኝነት ከንግሥት ቪክቶሪያ ጋር ያደርጓቸው መጻጻፎች ሁሉ ሰላማዊና ተስፋ የሚጣልበት ነበር። በዚያን ወቅት ከንግሥት ቪክቶሪያ የክብር ስጦታዎች መጥተውላቸዋል። ጆን ቤልና ፕላውዴን እንደ አንድ የጦር ወታደር ለአፄ ቴዎድሮስ  ወግነው ሲዋጉ ምንም እንኳን በተለያየ ጊዜ ቢሆንም ሁለቱም በጦርነት ሕይዎታቸው አለፈ። ሁለቱ የንግሊዝ ዜጎች በመሞታቸው አፄ ቴዎድሮስ በከፍተኛ ደረጃ ሀዘን ተሰማቸው። ተስፋ የመቁረጥ ስሜትም ታየባቸው።

ከዚያ በኋላ እራሳም፤ ካሜሮንና እስፒዲ የሚባሉ ቆንስላዎች ከንግሊዝ ሀገር የተላኩ ቢሆንም ለንጉሱ ተስማሚ ሆነው አልተገኙም። አማካሪነታቸውም ንጉሡን የሚያረካና ታማኝነት ያለው አልነበረም። በተለይም ካሜሮን አፄ ቴዎደሮስ ለንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉትን የመልካም ግኙኝነት ደብዳቤ በተገቢው ጊዜ እንዲደርስ ካለማድረጉም በላይ ደብዳቤው እንደደረሰ አስመስሎ ዋሽቶ ስለነገራቸውና መልስ አመጣለሁ እያለ ብዙ ጊዜ በማባከኑ፤ የንግሥት ቪክቶሪያ ምላሽ በመዘግየቱ ምክንያት በአፄ ቴዎድሮስ ዘንድ እንደ ንቀት ተቆጥሮ መካሪ የማይደፍረው ሽማግሌ የማይገባበት ኃያል ቁጣን አስከተለ። ከቪክቶሪያ መንግሥት ጋር ያለው ግኙኝነትም እየሻከረ መጣ። ራሳምና ካሜሮን፣ ሌሎችም በጋፋት የመድፍ ሥራ ላይ የነበሩት በሙሉ እንዲሁም ግብጻዊዩ ጳጳስ አቡነ ሰላማ ጨምሮ መቅደላ አፋፍ ላይ በእግር ብረት ታሠሩ። ይህ ታሪክ ነጮች ለመጀመሪያ ጊዜ በጥቁር ሕዝብ የማረሚያ ቤት ቁጥጥር ሥር የዋሉበት የታሪክ ዝክረ ነገር ሆኖ ሊታወስ የሚገባው ነው።

ጋፋት በወቅቱ ከአፄ ቴዎድሮስ ዋና ከተማ ከነበረችው ደብረታቦር ስድስት ኪሎሜትር እርቀት ላይ የምትገኝ ቦታ ናት፤ በአፍሪካዊያን ታሪክ ውስጥ ነጮች ለመጀመሪያ ጊዜ ወርሃዊ ቀለብ/ደመወዝ/ እየተከፈላቸው በጥቁር አሠሪ ተቀጥረው ከቁርጥራጭ ብረት አቅልጠው ከአፈር አንጥረው መድፍ ሠርተው እንዲያቀቡ የተሰጣቸውን መመሪያ ተግባራዊ ያደረጉበትና ታላቁ ሴቫስቶፓል መድፍ የተሠራበት ቦታ ነው።

አፄ ቴዎድሮስ የእንግሊዝ ሀገር ተወላጅ እስረኞችን እንዲፈቱ በተደጋጋሚ ከንግሥት ቪክቶሪያ መንግሥት ደብዳቤ ቢላክላቸውም ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም። በዚህ ምክንያት የተፈጠረው ግጭት እየከረረ መጥቶ እንግሊዝ እስረኞቹን ለማስፈታት በሚል ምክንያት በጀነራል ናፒር መሪነት በሰለጠነ ጦር መሳሪያ የሚታገዝ ሰራዊት ወደ ኢትዮጲያ አዘመተች።

የእንግሊዝ ጦር ዙላን ተሻግሮ በሰሜናዊ የሀገራችን ክፍል ትግራይ እንደ ደረሰ ጠምቀው ጋግረው በደስታ የተቀበሉት የተንቤኑ ተወላጅ የትግራይ ሹም የነበሩት ደጃዝማች ካሳ ምርጫ ነበሩ። ደጃዝማች ካሳ ምርጫ/ አባ በዝብዝ/ በኋላ አፄ ዮሐንስ 4ኛው፤ ጀነራል ናፒርን ተቀብሎ ከማስተናገድ በተጨማሪ የራሳቸውን የተሸለሙች በቅሎ ሰጥተው እስከ መቅደላ መቃረቢያ ዳሞትና ወርቀውሃ ድረስ መንገድ ጠራጊ ሆነው ይረዱ ነበር። በመጨረሻም ጦርነቱ ተካሄዶ ውጊያው ተፋፍሞ ከቆየ በኃላ ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀው የእንግሊዝ ጦር ድል ቀንቶት ብዙ የአፄ ቴዎደሮስ ምርጥ የጦር አበጋዞች እነ ፊታውራሪ ገብርየ/ የጋይንቱ ተወላጅ/ የመሳሰሉት ለሕይወታቸው ምንም ሳይሳሱ **«የታጠቅ አሽከር»** እያሉ ግንባር ለግንባር ከንግሊዝ ሠራዊት ጋር ተዋግተው ተሰው። በመጨረሻም አፄ ቴዎድሮስ እጃቸውን ከመስጠት ሞትን መርጠው የወገባቸውን ሽጉጥ መዘው እራሳቸውን አጠፉ።

የትግራዩ ደጃዝማች ካሳ ምርጫ የናፒር ጦር ደጋፊና መንገድ ጠራጊ ሆነው የአፄ ቴዎድሮስን ጦር በእንግሊዞች እንዲፈታ፤ የንጉሡም ሞት እንዲፋጠን ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም ወይም ሙት ወቃሽ አያሰኝም። በኋላም የእንግሊዝ ጦር ኢትዮጵያን ለቆ ሲወጣ ላደረጉት ውለታ ብዙ የጦር መሣሪያ ተሰጥቷቸዋል ቀደሞውኑ በተገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት አፄ ዮሐንስ 4ኛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሆነው ነገሡ።

ንጉሥ ምኒሊክ ገና በአሥራ ሁለት ዓመታቸው ሸዋን ለማስገበር የዘመቱት አፄ ተዎድሮስ በምርኮ መልክ ወደ መቅደላ አንባ አግዘዋቸው ነበር ሆኖም በንጉሡ ዘንድ እንደ ግዞተኛ ሳይሆን እንደ ልጅ ሥርዓተ መንግሥትን እየተማሩ በእንክብካቤ ያደጉና በኋላም አልጣሽ ቴዎድሮስን አግብተው ለሰባት ዓመታት አብረው የቆዩ ቢሆንም፤ በአጎቶቻቸው በእነራስ ዳርጌ ሣህለሥላሴ ምክንያት ከመቅደላ አንባ ሳይታሰብ ከድተው የባታቸውን ግዛት ሸዋን መልሰው የያዙበት ወቅት ነበር። የሸዋው ንጉሥ

ምኒሊክም/አባ ዳኘው/፤እንግሊዝ በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ያደረገውን የጦርነት ዘመቻ እያወቁ፣ ደጃዝማች ካሳ ምርጫ መንገድ ጠራጊ መሆናቸውን ሰምተው እንዳልሰሙ ሆነው፤አፄ ቴዎድሮስ ዜና እረፍት እስኪሰማ ድረስ ድምጣቸውን አጥፍተው ፀጥ ብለው ተቀመጡ።

እንግሊዞች አፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ አንባ ላይ ያከማቹትን ቅርሶች፣ መጽሐፍት፣ የወርቅ ዘውዶች፣ በጠቅላላው ውድ የሆኑ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት በሁለት መቶ በቅሎና በአሥራ አምስት ዝሆን ጭነው ዘርፈው ሲመለሱ፣ የሰባት ዓመት ልጃቸውን ልዑል ድጃዝማች ዓለማየሁ ቴዎድሮስን ማርከው ሲወስዱ፤ አፄ ዮሐንስም ሆነ ንጉሥ ምኒልክ፤ ንብሩቱ የሀገር ቅርስ ነው ወንዝ አይሻገርም። ደጃዝማች ዓለማየሁም ወገናችን ነው ተማርኮ በባዕድ ሀገር በግዞት አይቀመጥም ብለው ጥያቄ አላቀረቡም። ይልቁን ሁለቱም  በየበኩላቸው አፄ ቴዎድሮስ ከወደቀችበት አንስተው አንድ ባደረጓት ኢትዮጵያ ላይ ሥልጣናቸውን ለማደላደል ብቻ ይጣደፉ ነበር።

ዛሬ እነዚያ የተዘረፉት የኢትዮጵያ ቅርሶች በእንግሊዝ ሙዚሞች ተደርድረው በአስደናቂ ሁኔታ የዓለም የቱሪስት መስብ ሆነው ይገኛሉ። የአንበሳው ደቦል ልዑል ደጃዝማች ዓለማየሁም ሀገራቸውን እንደናፈቁ፣ በጥቁርነታቸው ተሳቀው ገና በ7ዓመታቸው የተለዩአቸውን አባትና እናታቸውን እያሰቡ ጠያቂ ዘመድ በሌለበት ደስተኛ ባልሆነ የብቸኝነት ሕይዎት ውስጥ እንዳሉ ዳግም የተወለዱበትን ሀገር አባታቸው የደከሙላትን ኢትዮጵያን ሳያዩ በተወለዱ በ19ዓመታቸው እንግሊዝ ሀገር ውስጥ አረፉ።

ከዚህ የታሪክ ዝክረ ነገር የምንረዳው ደጃዝማች ካሳ ምርጫ /አፄ የሐንስ/ና ንጉሥ ምኒሊክ ኃይላቸውን አስተባብረው አንድነታቸውን አጠንክረው ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር አብረው የናፒርን ጦር ቢመክቱ ኖሮ ምናልባት ኢትዮጵያ ገናናውን የቪክቶሪያን መንግሥት ድል አድርጋ የመለሰች ታላቅ ሀገር፤ አፄ ቴዎድሮስም እሩቅ የሆነው ዓላማቸውና ርዐያቸው እውን ሆኖ ገናናነታቸው በዓለም የታሪክ ማኅደር ይበልጥ የቀዳሚነቱን ድርሻ ሊዝ ይችል ነበር። ሆኖም የታሰበው ሳይሆ አፄ ቴዎድሮስ በሚያሳዝንና ለኀሊና በማይጠፉ መልኩ እሩቅ አሳቢ እቅርብ አዳሪ ሆነው ቀሩ።

አፄ ዩሐንስ ምንም እኳን ከእንግሊዞችን በተደረገላቸው ድጋፍ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥታቸውን ቢያጸኑም፤ በውስጣቸው የአፄ ቴዎድሮስን ዓላማ የሚያንፀባርቁ የሀገር አንድነት የማስጠበቅ ፍቅራቸው ከጠንካራ ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ጋር የተቆራኘ ነበር። የጎንደርን ሕዝብ ለማስደሰት ይሁን በሌላ፤ ቤተ መንግሥታቸውን ከተንቤን ትግራይ  ወደ ጎንደር፣ ደብረታቦር ጋፋት አዛውረው ጎሩይ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያንን አስተክለው ለትንሽ ጊዜ ኖረዋል።

በዚህ ጊዜ የጎንደር በጌምድር ሰው ንጉሡን በታላቅ ንጉሳዊ ክብርና ድጋፍ ተቀበላቸው እንጅ ክፉ ፊት አላሳያቸውም ነበር። አፄ ዮሐንስ ለእየ ጠቅላይ ግዛቱ የንጉሥነት ማዕረግ እየሰጡ ሲሾሙ፤ በንጉሠ ነገሥታቱ መናገሻ ታላቁ ሀገር ጎንደርን ሌላ ንጉሥ አይመራውም እኔው እራሴ እሾምበታለሁ ብለው እራሳቸው ይመሩት ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጥ የጎንደር ሕዝብ ንጉሡን ተከትሎ የመጣውን ትግሬ አንዱ ጨቋኝ ሌላው ተጨቋኝ ሳይሆን ተከባብረው በአንድነት መኖራቸውን ያስረዳል። የዛሬን አያድርገውና።

በመጨረሻም ድርቡሽ በሱዳን በኩል ዘልቆ በመግባት ወደ መሀል ጎንደር በሚገሰግስበት ወቅት መተማ ላይ በተደረገው ጦርነት እራሳቸው በግንባር እየተዋጉ በአስደናቂ የሀገር ፍቅር ስሜት ሕይዎታቸው አልፏል። ድርቡሽ የንጉሡን እራስ ቆርጦ በመውሰድ እስከ ዛሬ ድረስ በሱዳን ካርቱም ከተማ ሙዜየም ውስጥ ይገኛል። ዛሬ የትግራይ ተወላጆች ከሱዳን ጋር አብረው ጎንደሬውን ያፈናቅሉታል፣ይገድሉታል።

የመጀመሪያውን ርዕስ ለማጠቃለል ኢትዮጵያ ለአንድ ምዕት ዓመት ማንነቷ ተረስቶ ከቆየው ከጨለማው የዘመነ መሣፍንት በኋላ እንደገና የቆመችው በአፄ ቴዎድሮስና በጎንደር አርበኞች በእነ

ፊታውራሪ ገብርየ ግንባር ቀደም ተጋድሎና በሌሎቹም አጋርነት በመሆኑ **ኢትዮጵያንና ጎንደርን ለይቶ ማየት ዓለም ያለ ኦክስጅን/እስትንፋስ ሕይዎት ይኖረዋል ብሎ ማሰብ ነው።** ከኢትዮጵያ የረጅም ታሪክ ቀንሰን ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ከተነሱ በኋላ **በእያንዳንዱ ጎንደሬ ስሜት ውስጥ የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ በደሙ ውስጥ የሚላወስ ኅዋስ ነው** ብሎ መናገር የሌሎችን ፍጹም ኢትዮጵያዊነት ለማኮሰስ የቀረበ ድፍረት ወይም አድሏዊነት ሳይሆ እውነት መመስከር መሆኑኑ መታውቅ አለበት።

# ወልቃይትና ጎንደር፤

ኢትዮጵያ የግዛት አንድነቷ ዳር ደንበሯ ተከብሮ የክፍላተ ሀገራት አስተዳደር ስራት ከተጀመረበት የታሪክ ዘመን ጀምሮ ከተከዜ በመለስ ወልቃይት፣ ጸገዴ፣ አርማጭሆ፣ ማይጸምሪ፣ ሁመራ፣ መተማ፣ ዳንሻ በሙሉ በሰሜናዊ ጎንደር ጠቅላይ ግዛት/ ክፍለ ሀገር ሥር ሲተዳደር የኖረ ነው። በቦታው ላይ ለረጅም ዘመን ሰፍሮ የኖረው ባለመሬቱ፣ የገጠር ባለቀየው አሁን በቅርቡ በመሚዲያ በስፋት እንደሚነገረው ከቀደሙ አባቶቻችን እነልዑል ራስ መንገሻ ስዩም በምስክርነት እንዳረጋገጡት፣ የሀገሬው ተወላጅ ለዓመታት አቤቱታውን ሲያሰማ እንደቆየው፣ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪክ እንደሚያውቀው በደስታ ሲዘምር፣ በመከራ ሲያለቅስ፣ በጀግንነት ሲያቅራራ ሲፎክር ከአንደበቱ ለይቶት የማያውቀው **የመሬቱ ባለእርስት ወልቃይት ጎንደር አማራ ነው።**

አንዳንድ አፈጠብ ሰዎች የወልቃይት ጎንደር ቦታዎች በትግራይ ቋንቋ ስም የሚጠሩ በመሆናቸው ቦታዎቹ ትግራይን እንጅ አማራን አይወክሉም ይላሉ። ይህ የተሳሳተና መሠረተቢስ መናኛ አባባል ነው።ትግራይ ለጎንደር አዋሳኝና ደንበርተኛ በመሆኑ እና የጎንደር ሕዝብ ግእዝን ለረጅም ጊዜ አስፋፍቶ በመግባቢያነት ይጠቀም ስለነበረ ከትግርኛ ቋንቋ ጋር ተወራራሽ ወይም ተመሳሳይ ስሞችን በአጋርነት ይጠቀማል።

**<u>ምሳሌ 1</u>**፦ የቤት ቁሳቁስ ብንወስድ ካራ፣ ሞጎጎ፣ ሞግድ/ሞግዲ፣ ፍንጃል...የሚባሉት በትግርኛም በጎንደሬ አማርኛም መጠሪያቸው አንድ ነው። በመካከለኛው የሀገራችን ክፍል አማርኛ ግን ቢላዋ፣ ምጣድ፣ አከንባሎ፣ስኒ ይባላሉ። ታዲያ እነዚህ መገልግያዎች የትግራይ ብቻ ናቸው ብሎ መናገር መወሰን ይቻላል? አይቻልም።

**<u>ምሳሌ 2</u>**፦ አፄ ምኒሊክ በስተደቡብ ምስራቅ ጦርነት ተነስቶባቸው ነበር። በዚያን ጊዜ ከጦር አበጋዞቻቸው መካከል በቁመታቸው ዘለግ ያሉ ዓይነ ግቡዕ የነበሩ የሐማሴን ተወላጆች ነበሩ። ሆኖም ጦርነቱ አይሎ የአፄ ምኒሊክ ጦር እየሞቱ ሲሄድ፤ በሰሜኑ የሀገራችን ባህል የሞተ ሰው ወዲያው መቀበር ስላለበት፤ አንዱ ጓደኛው አንተ **ወደይ** እንቅበር እንጅ? ብሎ ሲጠይቀው፤ የለም ጦርነቱ አይሏል አሁን እንዋጋ **ቀብር በኋላ** ነው፤ በትግርኛ **ቀብሪ ዳህሪ** ብሎ መለሰለት። በዚህም መሠረት ወደ ሐረር በኩል በሚወስደው ቦታ ላይ ያለችው ከተማ በትግረኛ ቋንቋ **ቀብሪዳህር** ተብላ ተሰየመች። ታዲያ ይህች ሀገር ዛሬ ጊዜ ተመችቶናል፣ ኃይል አግኝቻለሁ፣ ጠያቂ ተሚጋች የለብንም ተብሎ በትግረኛ ቋንቋ ስያሜ ትጠራለችና ነባሩን ሕዝብ እያፈናቀሉ መብቱን እየረገጡ የትግራይ ተወላጆች ብቻ ባለመሬት ርዕስት ጉልት ማድረግ ይቻላል? አይቻልም። በጠቅላላው የማንነቱ መገለጫ የሆነው አማርኛን አጥብቆ አስረግጦ የሚናገር፣ በዳንሻና በሥናር ሱዳን ጥግ አዋሳኝ የሆኑት መጠነኛ አረብኛ የሚናገሩ፤ ለትግራይ ክፍለ ሀገር ጥግ አዋሳኝ የሆኑት ከዋነኛ የመቀሌና የአክሱም ትግርኛ ቋንቋ ይልቅ ለግእዝ ቅርብ የሆነ ትግርኛ ለመግባቢያነት የሚናገሩ፤ የአንድ እርሻ እሸት የሚበላ፣ የአንድ ወንዝ ውሃ የሚቀዳ፣ በአንድ ሜዳ ላይ የሚጫወት፣ በአንድ ዳስ የሚያሠርግ፣ በአንድ ድንኳን የሚያዝን፣ የአንድ ላም ወተት የሚጠጣ፣ ቀንበር ሞፈሩ ከተከሻው የማይለይ አራሽ ገበሬ ጠመንጃው ከደረቱ

የማይጠፋው አርበኛ **ወልቃይቴው ጎንደሬ** አማራ እንጅ የአክሱም፣ የመቀሌ፣ የአዲግራት፣ የተንቤን፣ የሽሬና የአድዋ ትግሬ ትግራይ ነው የሚል ማስረጃ ከየትም ሊገኝ አይችልም። ትግራዮችም ከተከዜ ባሻገር ለትግራይ ግዛት/ክልል የሚገባ እርስት ጉልት መሬት አለን ብለው የጠየቁበት፣ አቤቱታ ያቀረቡበት ወይም አመጽ ያነሱበት የታሪክ አጋጣሚ የለም።

# ትግራይና ጎንደር፤

*ሀገራችን ኢትዮጵያ ጥልቅ በሆነ ታሪኳ ውስጥ በትግራይ ተወላጆች ስትመራ ይህ የመጀመሪያው አይደለም የመጨረሻው ሊሆንም አይችልም። ትግራይን ከኢትዮጵያ ለይቶ ማየት እራስ የሌው አካል ወይም ሥነ ተፈጥሮአዊ ጉድለት ያለው ፍጡር ይሆናል። በቀደመው ታሪካችን ሀገራችን ኢትዮጵያን በፍቅር አንድነት አስደናቂ በሆነ መንግስታዊና ሃይማኖታዊ አመራር ላይ ለረጅም ዘመናት በአስተዳደሩ ነገሥታት እነአፄ ገብረ መስቀል፣ እነንጉሥ አርምሐ በቤተ መንግሥቱ የሚጠቀሱ ጥንታዊ መሪዎች ሲሆኑ በሃይማኖቱ በኩልም እነብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አረጋዊ ዘደብረ ዳሞ እነቅዱስ ያሬድ ዘአክሱም፣በቅርብ ጊዜ ታሪካችን ደግሞ እነ አፄ የሐንስ፣ ታላቁ አርበኛ እነራስ አሉላ አባነጋ ከትግራይ አብራክ የተገኙ የኢትዮጵያ ታሪክ በሕይዎት የመኖር እስትንፋሶች፣ ጌጦችና ፈርጦች ናቸው።*

ትግራይ ለጎንደር በባህል፣ በቋንቋ፣ በንግድ፣ በአጎራባች ደንብርተኝነት፣ በደስታም ሆነ በመከራ ተወራራሽ ክፍሎች ናቸው። **የትግራይ ሕዝብ ተስማምቶ መኖር ይችላል ከተባለ ከጎንደሬ የቀረበ ሌላ ዘመድ የለውም።** ጎንደሬውም ከትግራይ ተወላጆች ጋር በአንድ ጽዋ ሲጠጣ በአንድነት ሲያመልክ የኖረ ሕዝብ ነው። ምንም እንኳን ጎንደሬው በትግራይ ክልል ውስጥ ባይኖረም የትግራይ ተወላጆች ግን በጎንደር ክፍለ ሀገር በሁሉም አቅጣጫ ውስጥ በስፋት ይኖራሉ። በነጻነትም ይሠራሉ ይማራሉ።

*በዚህ ታሪክ ውስጥ ጎንደሬው ትግራዩን በማግለል ያደረገው አንድም በደል የለም። ይልቁንም የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅን ጨምሮ ሊላው ጎንደሬ ቢጠየቅ የቆየ ዘራችን ቢቆጠር ግማሼ የትግሬ የዘር ሐረግ አለኝ የማይል ጎንደሬ የለም። በመሆኑም የትግራይ ተወለጆችንም ሆኑ ኤርትራዊያን በትግርኛ ተናጋሪነታቸው አንድ አካል አድርጎ ሲመለከታቸው የኖረ ህዝብ ነው። በእውነቱ በመንፈሳዊ ትምህርት ቤትም ይሁን በዘመናዊ፣ በጎንደር ክፍለ ሀገር ክልል ውስጥ ለረጅም ዘመን የኖረ አንድ ሡርቶ አደር ትግሬ ወይም ኤርትራዊ ተወላጅ ጎንደሬው በትግሬነቴ/በኤርትራዊነቴ ለይቶ በደል አደረሰብኝ ብሎ የተከፋ ይኖራል ብሎ ቀርቶ መገመት ፍጹም ማሰብ አይቻልም።*

*ጎንደር ክርስትና በጥልቀት የተሰበከበት የሀገራችን ክፍል እንደመሆኑ መጠን ሕዝቡ እንግዳን ተቀብሎ ማስተናገድ የእምነቱ ዋነኛው ክፍል አድርጎ የኖረ ነው። በዕለት ሰንበት ጠምቆ ጋግሮ በዛፍ ጥላ ሥር ቁጭ ብሎ* ***በሞቴ አፈር ስሆን ብሉልኝ ጠጡልኝ*** *እያለ መንገደኛውን የሚያስተናግድ ገራገር እንጅ በቀለኛ ሕዝብ አይደለም።በአንድ ወቅት ፓሪስን ያላየ የፈረንሳይ ገበሬ፤ ጎንደርን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ትብሎ የተነገረበት ወቅት ነበር። ይህም ለሕዝቡ እንግዳ ተቀባይነት ለባህላዊ ውበቱ ዋና ምስክር ነው።*

*በዚያው መጠን ምንም ቢቸግረው በባህሉ፣ በሃይማኖቱ፣በአትንኩኝ ባይነት ጎንደሬነቱ ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያዊነቱ የሚያኮራው ሕዝብ ነው። ጎንደር ለእረጅም ዘመናት የትምህርት ማዕከል ሆኖ የቆየ እንደመሆኑ መጠን ከአራቱም ማዕዘናት የሀገራችን ክፍል የሚመጡትን ተማሪዎች በመንፈሳዊ እንግድነት ተቀብሎ ሕብረተቡ ከበሰለው እያካፈለ፣ከተረፈው እያለበሰ ሲያስተምር የቆየ ሀገር ነው።*

*በቅርቡ ፕሮፌሰር ማሞ ሙጬ የተባሉ ሙሁር በአንድ ወቅት በጎንደር ከተማ ቤተ መንግሥት ውስጥ የኦሮምኛ ቋንቋ ይነገር ነበር ብለው ጽፈዋል።እረግጥ ነው። በጎንደር የረጅም ታሪክ የየጁ አሮሞዎች በንጉሣሳዊ አስተዳደሩ ላይ ሥልጣን ይዘው ነበር። እነ እቴጌ መነን፣ እነራስ አሊ ሊበን ልጃቸው የአፄ*

ቴዎድሮስ ባለቤት እቴጌ ተዋበች አሊ ጨምሮ በጎንደር የኖሩ ኦሮሞዎች ናቸው። ጎበና የሚለው የኦሮምኛ ስያሜ በጎንደር ቁጥር ስፍር የለውም። አሁንም በርግጠኝነት የምንናገረው ቢኖር **የኢትዮጵያ አንድነት በጎንደሮች ሐዋርያነት ተሰብኳል ብሎ ደፍሮ መናገር ከጠባብነት የመጣ አስተሰብ ሊሆን አይችልም።** የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ከስያሜውምና ከተግባሩ እንደምንረዳው መላውን ትግራይን የማይወክል ግን ትግራይን መሠረት አድርጎ የተነሳ እንጅ ኢትዮጵያዊ አንድነትን የሚያንጸባርቅ አይደለም። ምናልባትም ከጎንደሬው ጋር ያለው አለመግባባት ከዚህ ጽንሰ ሐሳብ ጋር ያለው ግጭት ሊሆን ይችላል ብሎ መገመቱ አግባብ ነው። ይህም **መታየት ያለበት ኢትዮጵያዊነት የሚለው የሁላችን መጠሪያ የማያጠቃልል በመሆኑ ከጽንሰ ሐሳቡ ጋር የነበረ ሙግት እንጅ ትግሬውን በትግሬነቱ ብቻ በመጥላት ተቃራኒ ሆኖ መቆም አይሆንም።**

የዛሬን አያድርገውና የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባር ከኤርትራ ነጻ አውጪ የሥጋ ዘመዶቻቸው ጋር በመረዳዳት፤ በተለይም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በደርግ የብሔራዊ ውትደርና ዘመቻ፣ በእናት ሀገር ጥሪ መዋጮ፣ በማይመጣጠን ሀገር ውስጥ ገቢ ግብር፣ ጥናት በጎደለው የመንደር የሠፈራ ጣቢያ፣ በተለይም በጎንደር እነሻለቃ መላኩ ተፈራ የሚባሉ አእምሯቸው ለሌሎች ሰዎች አስተሳሰብ አስገዝተው የራሳቸውን ወገን በኢሕአፓ ምክንያት እሳት የጎረሰውን፣ በካል ብቃት የታነጸውን፣ በሀገር ፍቅር ስሜት የሚቃጠለውን፣ ለሰለጠነ ሕዛባዊ አስተዳደር መዋቀር የሚያፈገመግመውን የሀገሬውን ወጣት ስለረሸኑት የሕዝቡ መከፋትና መነሳቆል....ሁሉ ተደማምረው የደርግን ውድቀት እንዲፋጠን አደረጉት። ከዚያም የታሪክ ግንዛቤ ጉደለት ያለበት፣ የጠባብነት ቫይረስ ያጠቃው የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር ለትልቁ የኢትዮጵያ ሀገር አስተዳደር ሥልጣን እንዲጨብጥ ትልቅ በር ተፍቶለት ከነቫይረሱ ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ሰተት ብሎ ገባ።

ከዚያም **የራስን እድል በራስ መወሰን-መገንጠል የሚለው** አንቀጽ በሀገሩ አንድነት በማይደራደረው በጎንደሬው ዘንድ ተርጓሜ ያጣ እንቆቅልሽ ሆነ። በጎንደሮች ዘንድ ብቻ ሳይሆን ይህ የገንጣይ አስገንጣዮች አንቀጽ በሁሉም ኢትዮጵያዊያን ዘንድ የተጠላና የተነቀፈ ከዘመኑ ጥንድ ባህልን ባንድነት ከመገንባት **Multicluchral Development** አንጻር ሥልጡን ያልሆነ ቆሻሻና ነቀርሳ የሆነ አፍራሽ አስተሳሰብ መሆኑ የታወቀ ነው።

ሆኖም **መቸም የዓሣ ዝላይ መልሶ ከውሃው ነው** እንዳለችው ገጣሚ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጠበንጃ አፈሙዝ አስተዳደር መልሶ ወደ ጠበንጃ አፈሙዝ በመሸጋገሩ እንዳይተነፍስ ስለተገደደ፤ የሕዝብ ውሳኔ ሳይጠየቅ ብዙ መዋለ ንዋይና የሰው ሕይዎት የፈሰሰባትን የሀገራችን ክፍል ኤርትራን አስገነጠለ። የባህር በራችንም አዘጋው። ከዚያም በኋላ ከስህተቱ ተምሮ መሻሻል ሲገባው እንደ መለኮታዊ ቃል የማይሻር የማይለወጥ አድርጎ በሕዛባችን ጫንቃ ላይ በአስገዳጅነት ለዘላለም ጫነበት። መጫን ብቻ ሳይሆን እየመረረው በግድ ውጦት እንዲቀመጥ ተደረገ። ይሁን እንጅ ውስጥ ውስጡን የተዳፈነ እረመጥ ሆኖ እስካሁን እያቃጠለው ይገኛል። ምናልባትም ቃጠሎውን የታገስነው ታላቋን ትግራይን እኪያስገነጥል ድረስ ይሆናል።

የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር ስያሜውን ወደ ኢሕዴግነት ቢለውጥም የራስን እደል በራስ መወሰንን እስከ መገንጠል የሚለውን መሪ ቃሉ አድርጎ ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ **ትግራይ እስክትለማ ሌላው ሀገር ይድማ** በሚል መርሆ የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት በሙሉ በቀን በጨለማ ወደ ትግራይ ተጓዘ። በተለይም በጎንደር ጤፍ፣ የጥራጥሬ እህሎች፣ በርበሬ፣ የባህር ዛፍ እንጨት አጣና፣ አፈር ሁሉ ሳይቀር በቀን በሌሊት ተዘርፏል። ከዚህ በከፋ ሁኔታም ታሪክ የማይረሳቸው የሚከተሉት ዘግናኝ ተግባራት ተፈጽመዋል፤

1ኛ/ መንግሥት በሃይማኖት፤ ሃይማኖት በመንግሥት ጣልቃ አይገባም ብሎ ካወጀ በኋላ መለስ ዜናዊ፣ ታምራት ላይኔ፣ አባይ ፀሐይየ እየመከሩ በቀን ከአሥር ጊዜ በላይ ስልክ በማስደወል ስብናቸውን የሚጋፉ የቃላት ውርጅብኝ በማውረድ ከርሰዎ ጋር አንሰራም እጦጦ ጋራ ላይ ወጥተው ይቀመጡ በማለትና በማዋከብ ታላቁን የቤተ ክርስቲያን ሊቅና መንፈሳዊ አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ጎንደሬ በመሆናቸው ብቻ ከመንበረ ፓትርያርክነታቸው አፈናቅለው፤ በምትካቸው የትግራይ አድዋ ተወላጅ አቡነ ጳውሎስን ከአሜሪካን ጠርተው ሾሙ። ያ አልበቃቸው ብሎ በግፍ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተጫኑት ጨካኙ አባ ጳውሎስ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ አሁንም በድጋሜ አባ ማትያስን የተባሉ የትግራይ ተንቤን ተወላጅ ከሜሪካን ሀገር ጠርቶ ሾመ፤ በመከፋፈል ካንሰር የተመረዘው ወያኔ የቤተ ክርስቲያንዋን ሲኖዶስና አማኙን ለሁለት ከፍሎ፤ **አማራውንና ኦርቶዶክሱን አከርካሪውን ሰብረነዋል እያሉ ባልተግራ አንደበታቸው በሕዝብ ላይ ይሳለቃሉ፤**

2ኛ/ የጎንደር ክፍለ ሀገር ከመተማ እስከ ገረገራ ያለው ሕብረተሰብ ከደርግ ጋር ወግነህ ነበር በሚል የቂም በቀል ዱላ በእጅጉ ተደበደበ። ደብረታቦር በአንድ መርፌ ብዙ በሽተኞችን በማከም፣ የኤዲስ ቫይረስ በመከተብ ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ ሕይወቱ እንዲጠፋ አድርገዋል። አንዳንድ ቤተሰቦች በሙሉ የቤተሰቡ ግንድ ከሥሩ ጠፍቷል። ሰው ታሞ በተለይም ወደ ሕክምና ጣቢያ ሂዶ የሚያገግምበት ሳይሆን የመሞት እድል እጣ ፈንታው የሆነበት የሀገራችን ክፍል ሆኖ ቆይቷል። በተጫማሪም መንገድ እንሠራለን በሚል ምክንያት ለዘመናት ጥረው ግረው ያፈሩትን መኖሪያ ቤት በማፍረስ መንገዱን ሁሉ በትራክተር አስቀድሞ ግልብጥብጥ አድርጎ በማረስ ከአራት ዓመታት በላይ በጭቃ ውስጥ እንዲዘቅጥ በማድረግ የቁም እስረኛ አድርጎ ቀጥቅጦታል። በጠቅላላው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለተፈጸመው እጅግ በጣም ከባድ የዘር ማጥፋት ወንጀል የአካባቢውን ሕዝብ ጠይቆ መረዳት ይቻላል፤

3ኛ/ በወልቃይት ፀገዴ በትግራይ አዋሳኝ በሆኑት መሬቶች የነበሩትን የጎንደር ሕዝብ በማፈናቀል፤ ወጣቶችን እንዳይወልዱ የማምከኛ ክትባት በመስጠት፤ የታመሙት ወደ ህክምና ሲሄዱ በአጣዳፊ እንዲሞቱ በማድረግ፤ በምትኩ በድንጋያማው የትግራይ ክልል የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆችን ገብሬዎችን በማስፈር፤ የሱዳን አዋሳኝ የሆነውን የጎንደር ክፍለ ሀገር የሱዳን ወታደሮች ያለምንም ጥያቄ ዘልቀው እንዲገቡ በመፍቀድ የጎንደሬውን ቤት በማቃጠል፣ ሀብት ንብረቱን በመዝረፍ፣ በመግደል ከቦታቸው ላይ አሳቆና አማሮ በማፈናቀል በምትኩ በትግራይ ቆላማና ድንጋያማ አካባቢ ይኖሩ የነበሩትን ገበሬዎች በማስፈር የጥጥ፣ የቀባት ምርት በገፍ የሚታፈስባቸውን የቀንድ ከብት እንደ አሸን የሚረባበትን ለም የጎንደር መሬት ምራባዊ ትግራይ በሚል ስይሞ ለመከለል ብዙ የዘር ማጥፋት ወጀል ተፈጽሟል፤

4ኛ/በጎንደር ክፍለ ሀገር በሚገኙ ከተማዎች ሁሉ ለሚኖሩት የትግራይ ተወላጆች ከፍተኛ ገንዘብ ያለድካም በመለገስ የግል ድርጅቶች ባለቤት እንዲሆኑ በማድረግ በኢኮኖሚ የበላይነትን ይዘው፤ ጎንደሬው በችግራቸው፣ በርሃብና በስደታቸ ወቅት ወገኖቼ እንኳን ደህና መጣችሁ ብሎ ከእርስቱ እያካፈለ ከሚበላው እየቆረሰ እዳላስጠጋቸው፤ የእነሱ ገባር ሆኖ ተወልዶ ባደገባት የትወልድ ቦታው በንቀት ሲደላቀቁና የእነሱ ተቀጣሪ ሆኖ የአካልም የሞራልም ውደቀትና ድካም እንዲደርስበት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፤

5ኛ/በባህላዊ የቤተሰብ አስተዳደግ ሥርዓት ውስጥ ጫት የሚቅም የተረገመና አጋንት የሚጫወትበት እንደ መርገም የሚቆጠርና፤ ጫት ሲቅም የተገኘ ወጣት ከቤተሰቡ አንድነት ይገለላል። ይህ ባህል ዳብሮ በኖረበትና ጫት በአስፀያፊነት በሚታይበትና ከነጭራሹም በማይታወቅበት በጎንደር ክፍለ ሀገር የጫት መርትን ከመሥራቁ የሀገራችን ክፍል በገፍ በማስገባት ወጣቱ ጎንደሬ በጫትና በሱሰኝነት የዛለ፣

የላሸቀና የማያስብ የአካል ብቃት ጥንካሬ የጎደለው ደካማ ዜጋ እንዲሆን አድርገውታል። እያደረጉትም ይገኛሉ፤

6ኛ/ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ ባህሉን፣ ሃይማኖቱን፣ ወጉን የማዳበርና የማስጠበቅ መብቱ የተጠበቀ ነው። የሚለውን የይስሙላ ሕገ መንግሥት እረግጦና አፍኖ ከመያዙም በላይ እራሱ በተፈጥሮው በባህሉ፣ በሃይማኖቱ፣ በሃይማኖታዊ ትምህርት ሊቅነቱ፣በሀገር ወዳድነቱ፣ በእንግዳ ተቀባይነቱ፣በዘማች አርበኛና የአርበኛ ልጅነቱ ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያዊ አንድነቱን በማፍቀር የሚንደላቀቀውን፣ ሳይነኩት የማንንም መብት የማይነካ ኩሩውን ጎንደሬ/ጎጃሜ፤ ያልታረመ አንደበት ያላቸውን ካድሬዎቹን መልምሎ በማሰማራት በባዶ እጉር የሚሄድ ኩራተኛ ጎንደሬ፣የፊውዳል ሥራዓት ነፋቂዎች፣ የደርግ ርዝራዦች፣ዘገምተኛ አዕምሮ ያላቸው፣ ጡረተኞ፣ የሻቢያ ተላላኪዎች፣ የትግሬው ጠላቶች በሚል ተራ የማገጠ ስድብ በሕዛባዊ መገናኛ ጭምር እነ ሚሚ ስብሐቱ የመሳሰሉ ጋለሞቶችንና ወሮበሎችን በማሰማራት ኢትዮጵያዊ ጎንደሬው ማንነቱን አኮስሶ ለማሳየት ያላደርገው ጥረት የለም፤

7ኛ/በሕግ እና በዳኝነት የሚያምነው የጎንደር አርማጭሆ ሕዝብ፤ ከልላችን ጎንደር ክፍለ ሀገር ባህላችን ወጋችን አማራ እንጅ ወደ ትግራይ የተካለልንበት ዘመን የለም፤ ሕገ መንግስታዊ መብታችን ይከበርልን እያለ ሕዝቡ ኮሚቴ አቋቁሞ ማስረጃ ጠቅሶ፣ ምስክር ነቅሶ፣ አቤቱታውን በማሰማቱ፤ **ሀገር በቀል የሀገርና የህዝብ ጠላት ሆኖ የተንሳው ወያኔ፤** ኮሚቴዎቹን ጠራርጎ አፈናቸው። የቀሩት የፍርድ ቤት መጥሪያ ሳይደርሳቸው፣ ማስተንቀቂያ ደብዳቤ ሳይጻፍላቸው በሰላም የሚኖሩትን ዜጋ ኮሎኔል ደመቀን ድንገት ሌሊት መኖሪያ ቤታቸውን ከበው **እጅህን ስጥ** አሏቸው፤ **እኔ ጎንደር ተወልጀ እጄን አልሰጥም።** በማለት ጭንብል ያጠለቀውን አፋኙን የወያኔ ትግራይ ግብረ ኃይል ቅንድብ ቅንድቡን እያሉ መለሱት። ለ25 ዓመታት በግፍ ሲደበደብ የኖረው የጎንደር ህዝብ ትግሥቱ አልቆ ሆ ብሎ በከፍተኛ የወንድነትና የአርበኝነት ስሜት መብቱን ለማስከብር ተነሳ። አሁንም እያፈኑ እየያዙ በችግር ጊዜ አብረው የኖሩትን ያከል ዛሬ በአሁኑ ሰዓት በጥጋብ ጊዜ **ትግራዮች በጎንደሬው ላይ** አምሮ ሊቀበለው ከሚችለው በላይ በሚዘገንን ሁኔታ ትውልድ የማይረሳው ግፍ እየፈጸሙበት ይገኛሉ።

ይህ በትግራይ ህዝብ ስም በኢትዮጳያ መግሥት የሥልጣን ኮርቻ የተፈናጠጠው የወያኔ ቡድን፤ **ለወጥ ሊያመጣ የማይችል፣ ጥላቻ፣ በቀል፣ ጠባብነት፣ እራስ ወዳድነት በደሙ ውስጥ የሚዘዋወር፣ በጥፋቱ የማያምን ለድርድር፣ ለስምምነት፣ ለመልካም አስተዳደር እራሱን የማያዘጋጅ እና እጅግ በጣም ታሪካዊ እውቀትን፣ ኢትዮጵያዊ አንድነት አጥብቆ የሚጠላ ነው። በየቀኑ በጥላቻና በሌሎች ዜጎች መቃብር ላይ የተመሠረተ የበላይነትና የተስፋፊነት ኮርስ ሲያዳብር የሚውል ጨካኝና ከሃዲ ቡድን ነው**። ከአምስት ሚሊዮን በላይ ካድሬዎችን አስልጥኖ በመላው ኢትዮጵያና በውጪ ሀገር አሰራጭቷል። ይህ ግብረ ኃይል ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለመግደል የተሰማራ ነው። አንድ ጊዜ ገብተህበታልና በሃይማኖት በባህል ተታለህ ለማመንታት ጊዜ እንዳይኖርህ። ወያኔዎች ባሉበት የህክምና ጣቢያ አትታከም፣ የጊዜውን መቸገር አይተህ የሚያከፋፍሉትን ዱቄት ጋግረህ አትብላ። ሌሎችንም የምግብ ፍጆታ ሁሉ ከመጠቀምህ በፊት ልዩ ጥንቃቄ አድርግባቸው። በእብሪት በጥጋብ ያለምንም ምክንያት **ጎንደሬው ጠላቴ ነው** ብሎ ተነስቷልና ወያኔ አይምርህም አንተም አትማረው። ወያኔን በትዕግሥት የተሸከምክበት ትከሻህ ተልጧል እንቢ፤በቃኝ በል። ከ**መይሳው ታጠቅ!!**